# እኛ እና እነሱ

(ከባላንገብ)

ኢሕአፓ የሚታገለዉ ለህግ የበላይነት ነዉ በመሆኑም ተተቹሁ ተጠየኩ አላለም አይልምም። ነገር ግን ብዙ ጊዜ የሚስተዋለዉ፣ የተጎዳዉን የሞተዉን፣ ሰቆቃ የደረሠበትን፣ ስየል የተፈፀመበትን፣ ለማሰብ የሚከብድ ስቃይ የተቀበለዉን፣ ተበዳዮን ሟቹን እና ተጉጅዉን ኢሕአፓን እንከሳለን፣ እንጠይቃለን የሚሉት፣ አንድም እራሳቸዉ ተጠያቂ መሆን የነበረባቸዉ ወንጀለኞች ናቸዉ። አለያም ተጠያቂነትን በዉርስ የተቀበሉ የሚመስላቸዉ እና ኢሕአፓ እራሱን መከላከል አልነበረበትም የሚሉ ቂሎች ናቸዉ። በወታደራዊዉ ደርግ ስየል የፈፀሙም ሆነ የወያኔ ባለሟል ሆነዉ በወገኖቻችን ደም የነገዱትን ከሃዲወች ለፍርድ የማቅረቡ እና የህግ የበላይነትን በተግባር የመተርጎሙ ጉዳይ በወያኔ ዉድቀት ማዕግስት በይደር የማይያዝ እና የማይታለፍ ሃገራዊ ግዴታ ነዉ። ያኔ ብቻ ነዉ ወደ ስልጣን መንበር የሚመጡ ሁሉ ለተግባራቸዉ ተጠያቂነትን እንዲቀበሉ ማስገደድ የሚቻለዉ። በርግጥ ይህ ሃሳብ የሚያንዘረዝራቸዉ የዕብድ ገላጋዮች ቁጥራቸዉ ትንሽ አይደለም። ሺፍንፍን ለምግብ እንደሆን እንጅ በሃገር ጉዳይ ቦታ የለዉም።

በእርቅ ስምም በግ እና የዱር ተኩላን ይላመዱ ማለት ተመሳሳይ ነገር በማድረግ የተለየ ዉጤት እንደመጠበቅ አይነት ነገር ነዉ። የኢሰፓዉ ተጠሪ እና የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሺነር የነበረዉ ሻለቃ ያኔም አሁንም ሰልፋቸዉ ከህዝብ አይደለም አልነበረምም። ባይሆን አሁን አይናቸዉን በጨዉ አጥበዉ ወዲ አፈወርቂ የኢትዮድያ አንድነት ጠበቃ ነዉ ይላሉ? አማርኛ ጠፍቶበት Vision ምናምን እያለ ዉትር ዉትር እሚለዉ ገልቱ ዶክተርም በትንሺ ነገር አኩሩፎ እስኪሄድ ድረስ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለቱ የሚጠበቅ ነዉ። ዶክተሩ እስከተጨበጨበለት ድረስ የማይባለዉንም የማይሆነዉንም ያላዝናል። አሳ በተራራ ዝንጀሮ በባህር መኖር አለባቸዉ ይልና እንዴ! እንዴት ተደርጎ አሳዉ የባህሩ ባለቤት ብቻ ሳይሆን ከባህሩ ከወጣ ህይወትም አይኖረዉ ለዛዉስ እርሱ መች በባህር አልኖርም አለ ሲባል። “ሲጀመር በእንግሊዝኛ እና በሃበሺኛ ሲታሰብ የተለያዮ ነዉ ደግሞም እኔ የማዉቃቸዉ በምኖርበት አካባቢ የሚኖሩ አሳወች ሁሉ በባህር መኖር እማይፈልጉ ናቸዉ። ደግሞም እኮ እኔ ዶክተር ነኝ!” ይላል። የጠያቂወች ልበሙሉነት ያንዘፈዝፈዉ እና “እንዳዉም የሆድ ቁርጠትም የያዘኝ በእናንተ ምክንያት ነዉ። እንኳን ደስ አላችሁ!” ብሎ በማይገናኝ ነገር ያሳርጋል።

የኢሠፓዉ ሰዉዮ እና ሻለቃዉ ግን ለምን እና እንዴትስ ነዉ ከወዲአፈወርቂ ጋር እሚገናኙት? ማግኘታቸዉ እና ማናገራቸዉን ባይክዱም ከመንግስት ስልጣን ከወረዱ በኋላ እና የሚታወቅ ማህበራዊ ሚና ሳይኖር አንጋሺ እና አናጋሺ መሆንስ የተወራዉን የሚያረጋግጥ ይሆን? ለሁሉም እስከዛ ዉሾችም ትልልቅ እና አደንቆሪ ጡሩንባቸዉን ይዘዉ መጮሃቸዉን አያቆሙም። ዳሩ መተዳደሪያስ አይደል። ባዕዳን አለቆቻቸዉም አይዞችሁ ይሏቸዋል። ጊዚያዊም ቢሆን አዛዥ ናዛዥ ለመምሠል ይጥራሉ። ከጡሩምባዉ የሚወጣዉ ድምፅ ብዙዉን ጊዜ ለጆሮ የሚቀፍ እና አሉታዊ ቢሆንም አንዳንዶች በጡሩንባዉ ትልቅነት እና ዉጫዊ ቀለሙ ተፅዕኖ ስር ይወድቁ እና ግራ ይጋባሉ። በወገን ደም እጃቸዉ የተበከሉትም መቃዠታቸዉ እና መወራጨታቸዉ የሚጠበቅ ነዉ። ወያኔም አጋጣሚዉን በመጠቀም በየህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሰርጎ ገቦችን ለማስረግ ትሞክራለች። የቅርብ ጊዜዉ የወያኔ ሰርጎ ገብ የመቀሌውን አቻምየለህ ታምሩን ምንደኛነት ልብ ይሏል።

የህዝብ ልጆች የሞት ሺረት ሁለገብ ትግል ያደርጋሉ። በመጨረሻም በሃገራችን ጉዳይ እጃቸዉን ያስገቡ ባዕዳን ሁሉ በተላላኪወቻቸዉ ተስፋ ይቆርጣሉ። ቀድሞውንም ለወንድሞቻቸው ያልታመኑ ብለውም ይፀየፏቸዋል። ጥሩምባዉም ድምፅ ያጥረዉ እና ይሰላል። ተከፋይ ጥሩምባ ነፊወችም በጥሩምባዉ ላይ ያድማሉ። ስራቸዉን ወደዉት እንደማያዉቁም በምሃላ ይገልፃሉ። epdaን ያስታዉሷል። ያኔ የህዝብ ልጆች ከወገኖቻቸዉ ጋር ስርየትን ያገኞሉ። እራሳቸዉን ነገረ ፈጅ አድርገዉ የሚያስቡ ባዕዳንም ምርጫ ያጡና ከተላላኪወቻቸዉ ይልቅ ከጠንካራ የህዝብ ልጆች ጋር መደራደርን ይመርጣሉ። ይህ ትንቢት አይደለም በተደጋጋሚ የታየ እዉነታን መሠረት ያደረገ ተጨባጭ ግንዛቤ ነዉ።

ከሃያ አምስት አመት ከፋፍለህ ግዛዉ አስተዳደር በኋላ ማን ይሙት ወያኔ እና አለቆቹ አዲሱ ትዉልድ ስለአንድነት እና ሃገራዊ ፋይዳ መሳሪያ ተደቅኖበት ባለሶስት ቀለሙን ምንም ያልታከለበትን እና ያልተቀነሰበትን ታሪክ ሰሪ አርበኞቻችን ከባህረነጋሺ እስከ ሞያሌ የወደቁለትን የጥቁር ህዝቦች ሁሉ ኩራት የሆነዉን ሰንደቃችን ያዉለበልባል ብለዉ ያልማሉ? በጭራሺ!! ለዛም ነዉ በድንጋጤ ተርበትብተዉ በአስር ሺወችን ለእስር የዳረጉት እና የአስቸኮይ ጊዜ ቅብጥርስ ያሉት። ኢትዮድያዊነት ምን

ያክል ቢቀጠቀጥ ሊጠፋ እና ሊተን እንደማይችል የቅርብም የሩቅም ጠላት ዛሬ ላይ በሚገባ ተረድቷል። ወያኔም ሃሳቡ ተመሠቃቅሎበት አንዴ ሰፈድ ሌላ ጊዜ ስለዮጋንዳ የከብት እርባታ ቢያወራ ከህዝብ ጋር ሆድ እና ጀርባ መሆኑን ጠንቅቆ ተረድቷል። የቀረዉ የዉድቀት ሰዋሠዉ የሆነዉ የመጨረሻ የጭካኔ በትርን በመጠቀም ለማሸማቀቅ እና በፍራቻ ለመሸበብ መሞከር ነዉ። ለዚህ ሌላ "ሃዉዜንን" አይነት መጠነ ሰፊ ፍጅት ሊያደርስ እና እንደተለመደዉ ፀረ ሰላም ሃይሎች ባደረሱት ጥቃት በርካታ የህይወት እና የንብረት ጥፋት ደረሰ ሊል እንደሚችል እና በቱጃሩ ሼክ በኩል ሌላ መቶ ሚሊዮን ሌላም ሌላም ሰብስቦ ገዳይም ሙሾ አዉራጅም ሊሆን እንደሚችል መጠበቅ የዋህነት አይሆንም። ይልቅስ ሃገር ወዳዶች እና ፍትህ ወዳድ ወገኖች ሁሉ ይህን አይነት መሠሪነት ቢፈፀም ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል የሚለዉን ማዉጠንጠን የሚገባቸዉ ይመስለኛል።